በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የመ.ቁ.196871

ሐምሌ 27/2013 ዓ.ም

ዳኞች፡ እትመት አሰፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሳዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡ አቶ ሀብታሙ ዝናቡ ፡- ቀርበዋል

ተጠሪ፡ አቶ ታሪኩ አየለ ፡- አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል

## ፍርድ

በዚህ መዝገብ ላይ የቀረበው ጉዳይ የከተማ ይዞታ ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/333779 ላይ ጥቅምት 03/2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት የስር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔን በማፅናት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት ለማስለወጥ ነው፡፡

ክርክሩ የተጀመረው የአሁን ተጠሪ ሐምሌ 05/2011 ዓ.ም ፅፈው በአሁን አመልካች ላይ በጅማ ወረዳ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ ነው፡፡ ፍሬ ቃሉም ቦታ እና አዋሳኙ በክሱ ዝርዝር ውስጥ የተጠቀሰውን 200 ካሬ ሜትር የከተማ ይዞታ ነሐሴ 06/2011 ዓ.ም ተሰጥቷቸው አስፈላጊውን ክፍያ ፈፅመው እና የግንባታ ፈቃድ አውጥተው በቦታው ላይ ግንባታ ለማከናወን ሲሄዱ ባላወቁት መንገድ የአሁን አመልካች ትንሽ ሰርቪስ ቤት ሰርተዉበት የያዙባቸው መሆኑን በመግለፅ በፍርድ ኃይል ተገደው በቦታው ላይ የሰሩትን ቤት አፍርሰው እንዲለቁላቸው ዳኝነት የሚጠይቅ ነው፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

አመልካች ለዚሁ ክስ በሰጡት መልስ ይዞታውን በ1987 ዓ.ም በሽንሻኖ ያገኘሁት ህጋዊ ይዞታዬ ነው፤ ተጠሪ ከክሳቸው ጋር ያቀረቡት ማስረጃም ይዞታውን የሚመለከት አይደለም፤ ተጠሪ ከአካባቢውም ምንም ይዞታ የሌላቸው በመሆኑ ልለቅ አይገባም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ በመስማት እና ስለጉዳዩም ከአስተዳደር ክፍሉ ተጣርቶ እንዲቀርብለት በማድርግ እንዲሁም ይዞታው ለተጠሪ ሲሰጥ ነበሩ የተባሉትን የክፍሉ መሬት አስተዳደር ባለሙያዎች የይዞታውን ማህደር ይዘው በመቅረብ ስለይዞታው አሰጣጥ እንዲያስረዱ ካደረገ በኋላ በሰጠው ውሳኔ ለክርክር ምክንያት የሆነው ይዞታ ቀደምት ይዞታነቱ የአሁን አመልካች ቢሆንም ይዞታው ከአምልካች ላይ በህጋዊ መንገድ ተወስዶ ለአሁን ተጠሪ በሽንሻኖ የተሰጠ መሆኑን፣ ይህ ሲሆንም በዞታው ላይ ዛፍ ብቻ እንጂ በአመልካች የተሰራ ቤት ያልነበረበት ስለመሆኑ አረጋግጫለሁ በማለት አመልካች በቦታው ላይ የሰሩትን ቤት አፍርሰው ይዞታውን ለተጠሪ ሊለቁ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡ ይኸው ውሳኔ እስከ ክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ ፀንቷል፡፡

የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡ አመልካች ጥቅምት 11/2013 ዓ.ም ፅፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ ተፈፅሟል ያሉትን መሰረታዊ የህግ ስህተት ጠቅሰው በዚህ ችሎት እንዲታረምላቸው ጠይቀዋል፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ለክርክር መነሻ የሆነው ይዞታ ለአሁን ተጠሪ ከመሰጠቱ በፊት የአመልካች ቤት የነበረበት መሆኑ ባልተካደበት አመልካች ቤቱን አፍርሰው ይዞታውን ለተጠሪ ያስረክቡ ተብሎ የተወሰነበት አግባብ ግራ ቀኙ በተገኙበት ለዚህ ችሎት ቀርቦ እንዲመረመር በመታዘዙ ግራ ቀኙ የፅሁፍ ክርክር እንዲለዋወጡ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት በአጭሩ ይህንን ሲመስል ችሎቱም የግራ ቀኙን ክርክር ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ እና በስር ፍርድ ቤት በማስረጃ ከተረጋገጠው ፍሬ ነገር አንፃር አግባብነት ካለው ህግ ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

እንግዲህ ከስር ፍርድ ቤት የመዝገብ ይዘት መረዳት እንደሚቻው ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ይዞታ ቀደምት ይዞታነቱ የአሁን አመልካች ቢሆንም ስልጣን ባለው አስተዳደር አካል ከአመልካች ተወስዶ አስተዳደር እጅ ከገባ በኋላ በህጋዊ መንገድ ለአሁን ተጠሪ በሽንሻኖ የተሰጠ ለመሆኑ ማስረጃን የመመርመር እና የመመዘን ስልጣን ባለው የወረዳው ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡ የይዞታውን አወሳሰድ በተመለከተም በይዞታው አካባቢ በተደረገ አሰሳ ከአንድ ሰው በቀር አመልካችን ጨምሮ በርካታ ሰዎች በአካባቢው ያለምንም ህጋዊ መብት መሬት ይዘው የነበረ በመሆኑ መንግስት ሰዎቹን በማሳመን ተቀብሏቸው በሽንሻኖ ለሌሎች ሰዎች የሰጠ መሆኑን እና በዚሁ አግባብ አሁን ክስ የቀረበበት ይዞታ ለተጠሪ የተሰጣቸው ስለመሆኑ በክፍሉ መሬት አስተዳደር ባለሙያዎች በዝርዝር መገለፁን የወረዳው ፍርድ ቤት መዝገብ ያሳያል፡፡ በይዞታው ላይ ለተጠሪ የተሰጠውን የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ ህጋዊነትን አስመልክቶ ትክክለኛው እና ህጋዊ ሰነድ በተጠሪው እጅ ያለው ሲሆን በመሬት አስተዳደሩ ጽ/ቤት በሚገኘው ቀሪ ላይ በጽ/ቤቱ ሰራተኛ ሆነ ተብሎ JU30P1 የነበረው 1 ቁጥሩን በካርቦን ፅሁፍ ወደ 4 ተለውጦ የተተካ ስለመሆኑ ተደርሶበት ሰራተኛው በስነ ምግባር የተረከሰሰ ስለመሆኑንም መረጋገጡ ተገልጿል፡፡

*ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

ከእነዚህ በፍሬ ነገር ደረጃ ከተረጋጡት ነጥቦች በግልፅ መረዳት የሚቻለው የአሁን አመልካች ለክርክር ምክንያት በሆነው ይዞታ ላይ ቀድሞውንም ቢሆን በህግ ጥበቃ የሚደረግለት የይዞታ መብት ያላቋቋሙ ሲሆን ይዞታው ስልጣን ባለው አስተዳደር አካል ከአመልካች ላይ ተወስዶ ለተጠሪ በሰነድ ተረጋግጦ የተሰጣቸው መሆኑን ነው፡፡ በፍሬ ነገር ደረጃ ይህ ከተረጋገጠ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ማስረጃን መሰረት ያደረገ ነው ከሚባል በቀር የሚነቀፍበት መሰረታዊ የህግ ስህተት የለም፡፡ በመሆኑም የአመልካች የሰበር ቅሬታ ውድቅ ተደርጎ ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ውሳኔ

የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/333779 ላይ ጥቅምት 03/2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት የስር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔን በማፅናት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡

## ትዕዛዝ

1. የዚህን ሰበር ሰሚ ችሎት ክርክር ወጪ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
2. በዚህ መዝገብ ላይ የተሰጠ የእግድ ትዕዛዝ ካለ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም